፲፬ ወደ ፡ ምድያም ፡ ሄድሁ ፡ የምድያም ፡ ክፍል ፡
በምትሆን ፡ በራጊስ ፡ ያለ ፡ ገባኤልንም ፡ ገንዘ
ቤን ፡ አደራ ፡ አስጠበቅሁት ፡፡
፲፭ ስልምናሶር ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ሥራው ፡ ክፉ ፡
የሆነ ፡ ሰናክሬም ፡ ስለሱ ፡ ፈንታ ፡ ነገሠ ፡፡ ከሹ
መቴ ፡ ሻረኝ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ምድ
ያም ፡ መሄድ ፡ አልቻልኩም ፡፡
፲፮ በስልምናሶርም ፡ ዘመን ፡ ለወንድሞቼ ፡ ብዙ ፡
ምጽዋት ፡ መጸወትሁ ፡፡
፲፯ እህሌንም ፡ ለተራቡ ፡ ሰዎች ፡ ሰጠሁ ፡ ልብሴ
ንም ፡ ለተራቆቱ ፡ ሰዎች ፡ ሰጠሁ ፡፡ ከወገኖቼ ፡
በነነዌ ፡ አደባባይ ፡ የሞተ ፡ ሰውንም ፡ ባይ ፡ እቀ
ብረው ፡ ነበር ፡፡
፲፰ ሸሽቶ ፡ ከይሁዳ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ሰናክሬም ፡
የገደላቸው ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩ ፡ ተቈጥቶ ፡ ብዙ ፡
ሰው ፡ ገድሏልና ፡ እኔ ፡ ተሠውሬ ፡ እቀብራ
ቸው ፡ ነበር ፡ ንጉሡም ፡ ፈልጎ ፡ ሬሳቸውን ፡
አላገኘም ፡፡
፲፱ ከነነዌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሄዶ ፡ እንደቀበርኋቸው ፡
ነገር ፡ ሠርቶ ፡ ከንጉሡ ፡ አጣላኝ ፡ ሊገድሉኝ ፡
እንዲፈልጉኝ ፡ በወቅሁ ፡ ጊዜ ፡ ፈርቼ ፡ ተሠ
ወርሁ ፡፡
፳ ባጡኝም ፡ ጊዜ ፡ ልጄ ፡ ጦብያና ፡ ሚስቴ ፡ ሐና ፡
ሲቀሩ ፡ ገንዘቤን ፡ ሁሉ ፡ በረበሩ ፡፡
፳፩ ሁለቱ ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ እስኪገድሉት ፡ ድረስ ፡
ሸሽተውም ፡ ወደ ፡ አራራት ፡ ተራራ ፡ እስኪ
ሄዱ ፡ ድረስ ፡ ፶፭ ፡ ቀን ፡ ከቤቴ ፡ አልወጣሁም ፡፡
ልጁ ፡ እስራደንም ፡ ስለርሱ ፡ ፈንታ ፡ ነገሠ ፡
የወንድሜ ፡ ልጅ ፡ የእናሔል ፡ ልጅ ፡ አኪአኪ
ሮስንም ፡ በሥራታቸውና ፡ በቤቱ ፡ ወገኖች ፡
ላይ ፡ ሁሉ ፡ ሾመው ፡፡
፳፪ አኪአኪሮስም ፡ ማለደልኝ ፡ ወደ ፡ ነነዌም ፡
መለሰኝ ፡፡ በቤቱ ፡ ጣጣና ፡ ማኅተም ፡ ለርሱ ፡
ያለ ፡ አኪአኪሮስም ፡ ዳግመኛ ፡ እክሮንድስን ፡
ሾመ ፡፡
፳፫ ወደ ፡ አገሬም ፡ በተመለስሁ ፡ ጊዜ ፡ ልጄ ፡ ጦብ
ያንና ፡ ሚስቴ ፡ ሐናን ፡ መለሰልኝ ፡፡

ምዕራፍ ፡ ፪ ፡፡

፩ ሰባተኛ ፡ ሱባዔ ፡ በምትሆን ፡ በከበረች ፡
በዓለ ፡ ፶ ፡ ለእኔ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አደረጉ ፡ እበላም ፡
ዘንድ ፡ ተቀመጥኩ ፡፡
፪ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ መሸ ፡ በየሁ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ አስቤዋለሁና ፡ ልጄን ፡ ሄደህ ፡ ከወንድሞ
ቻችን ፡ ያገኘሃቸውን ፡ ድኆች ፡ ሰዎችን ፡ አምጣ ፡
እነሆ ፡ እኔ ፡ እጠብቅሃለሁ ፡ አልሁት ፡፡
፫ በተመለሰም ፡ ጊዜ ፡ ከወንድሞቻችን ፡ የሞተ ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘሁ ፡ ሬሳውም ፡ በደባባይ ፡
ወድቋል ፡ አለኝ ፡፡
፬ እኔም ፡ እህል ፡ ሳልቀምስ ፡ ተነሥቼ ፡ ፀሐይ ፡
እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቤት ፡ አገባሁት ፡፡
፭ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ተመልሼ ፡ ታጥቤ ፡ እያዘንሁ ፡
ራቴን ፡ በላሁ ፡፡
፮ አሞፅ ፡ በዓላችሁ ፡ ወደ ፡ ኀዘን ፡ ተድላችሁ ፡ ደስ
ታችሁም ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፡ ይመለሳል ፡ ያለውን ፡
አሰብሁ ፡፡
፯ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አለቀስሁ ፡ ፀሐይም ፡ በገባ ፡
ጊዜ ፡ ሔጄ ፡ መቃብር ፡ ቆፍሬ ፡ ቀበርሁት ፡፡
፰ ንጉሥ ፡ የገደላቸውን ፡ ይቀብራልና ፡ ስለዚህ ፡
ሥራ ፡ እንዳይገድሉት ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ አይፈራ
ምን ፡ ብለው ፡ ሳቁብኝ ፡፡
፱ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሆኜ ፡ በድ
ሞው ፡ ሥር ፡ ተኛቼ ፡ አደርኩ ፡ ዓይኖቼ ፡ ግን ፡
ተገልጠው ፡ ነበር ፡፡
፲ በድሞው ፡ ላይ ፡ ወፎች ፡ እንዳሉ ፡ አላወቅሁም ፡
ፌቱ ፡ ተገልጦ ፡ ሳለ ፡ እለዚያ ፡ ወፎች ፡ በዓይኔ ፡
ላይ ፡ ትኩስ ፡ ፋንድያ ፡ ጣሉብኝ ፡ በዓይኔ ፡ ብልዝ ፡
ብጉር ፡ ወጣብኝ ፡፡ እኔም ፡ ወደ ፡ ባለ ፡ መድኃ
ኒት ፡ ሄድኩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የጠቀመኝ ፡ የለም ፡፡
ብቻየን ፡ ወደ ፡ ኤልማድያ ፡ እስከሄድ ፡ ድረስ ፡
አኪአክሮስ ፡ ይመግበኝ ፡ ነበር ፡፡
፲፩ ሐናም ፡ በሴቶች ፡ ቤት ፡ ታገለግል ፡ ነበር ፡፡
፲፪ ወደ ፡ እመቤቶቿ ፡ ላከች ፡ እነዚያም ፡ አንዲት ፡
የበግ ፡ ጠቦት ፡ ሰጧት ፡፡
፲፫ ወደኔ ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ ትጮህ ፡ ጀመር ፡ ይቺን ፡
ጠቦት ፡ ከወዴት ፡ አመጣሻት ፡ አልኋት ፡፡ የተ
ሰረቀ ፡ ገንዘብ ፡ መብላት ፡ አይገባምና ፡ የሰረቅ
ሺውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጌቶቹ ፡ መልሺው ፡
አላት ፡፡
፲፬ ስለ ፡ ደሞዜ ፡ ፈንታ ፡ ሰጡኝ ፡ አለችኝ ፡ እኔ ፡
ግን ፡ አላመንኋትም ፡ ለባለቤቶቹ ፡ መልሺ ፡
ብዬ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ተከራከርሁ ፡፡ እርሷም ፡
መልሳ ፡ ምጽዋትህና ፡ ጸሎትህ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡
እነሆ ፡ በላይህ ፡ ያለ ፡ ኃጢአትህ ፡ ሁሉ ፡ ታወቀ ፡
አለችኝ ፡፡

ምዕራፍ ፡ ፫ ፡፡

፩ በልቡናዬ ፡ ኀዘን ፡ ተከዝሁ ፡ ጸለይኩ ፡ አለቀ
ስሁ ፡፡
፪ አቤቱ ፡ በሥራህ ፡ ሁሉ ፡ በፍርድና ፡ በቸርነት ፡
በሚገባ ፡ እውነትም ፡ አንተ ፡ እውነተኛ ፡ ነህ ፡
አልሁ ፡፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ በሚገባ ፡ ዓለምን ፡ ትገ
ዛለህ ፡፡
፫ አስበህ ፡ በዓይኔ ፡ ምሕረት ፡ ተቀበለኝ ፡ አንተን ፡
በበደሉ ፡ ትእዛዝህንም ፡ ባልሰሙ ፡ በአባቶቼ ፡
ኃጢአትና ፡ በኃጢአቴ ፡ ተበቅለህ ፡ አታጥፋኝ ፡፡
፬ ለመማረክና ፡ ለመበርበር ፡ ለሞትም ፡ አደረግ
ኸኝ ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ በነርሳቸውም ፡ ዘንድ ፡
በተበተንባቸው ፡ በአሕዛብ ፡ አገር ፡ ተግዳሮት ፡
ለመስማት ፡ መተረቻ ፡ ሆንን ፡፡
፭ አሁንም ፡ በእውነት ፡ የሚፈረድ ፡ ፍርድህ ፡
ብዙ ፡ ነው ፡ ትእዛዝህን ፡ አላደረግንምና ፡ በፊ
ትህም ፡ በውነት ፡ ጸንተን ፡ አልኖርንምና ፡ ያባ
ቶቼና ፡ የእኔ ፡ ኃጢአት ፡ በሚሠረይ ፡ ገንዘብ ፡
አድርግልኝ ፡፡
፮ አሁንም ፡ በፊትህ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝህን ፡ ነገር ፡
አድርግ ፡ ከመኖር ፡ ሞት ፡ ይሻለኛልና ፡ በሞት ፡
እሰናበት ፡ ዘንድ ፡ መሬትም ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡

